# ጊዜአዊ ፡ አከራካሪ ፡ አስተያየት ፤

## ስለወንጀል፡ ይግባኝ ፡

(የይግባኝ ፡ ብዛት—የምክር ፡ ቤት ፡ ፍላጎት ፡ (ሐሳብ) ፡ እና ፡ እንዴት ፡ እንደተፈጸመ— ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ የማይፈቀድባቸው ፡ ሁኔታዎች—የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቍጥር ፡ ፩፻፺፭ (፪) ትርጉም—የይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለፍትሕ ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፣ ስለቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ እና ፡ ስለሁለቱ ፡ ፍትሕና ፡ ቅጣት ፡ ውሳኔዎች ፡ የይግባኝ ፡ ሥልጣን) ።

### መግቢያ ።

በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) መሠረት ፤ ስለ ወንጀል ፡ ክስ ፡ ሁለት ፡ ይግባኝ ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ። ይኸውም ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቢጀመር ፤ ይግባኙ ፡ ለአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመጀመሪያ ፡ ይግባኝ ፡ ቀርቦ ፡ ካስፈለገ ፡ እንደገና ፡ በሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ከአውራጃ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊወሰድ ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከአንቀጹ ፡ ጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ ይህንን ፡ ሐሳብ ፡ ለማግኘት ፡ ቢቻልም ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) ከዚህ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ አስተያየት ፡ ስላለ ፡ የይግባኝ ፡ አወሳሰድ ፡ ዘዴ ፡ ሁልጊዜ ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ ብቻ ፡ ተወስኖ ፡ ሊፈጸም ፡ አይችልም ።

(ይህ ፡ እንዴት ፡ ሊሆን ፡ እንደሚችል ፡ ከመግለጻችን ፡ በፊት ፤ የወንጀል ፡ ፍርድ ፡ በስንት ፡ ደረጃ ፡ ሊከፈል ፡ እንደሚችል ፡ መረዳት ፡ ይኖርብናል ። በማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሚሰጥ ፡ የተሟላ ፡ የወንጀል ፡ ፍርድ ፤ ሁለት ፡ ዋና ፡ የፍርድ ፡ አስተያየቶችንና ፡ ውሳኔዎችን ፡ የያዘ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ አንደኛ ፤ የወንጀለኛው ፡ ጉዳይ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ተጠንቶና ፡ ተመዛዝኖ ፡ ጥፋተኛ ፡ መሆኑን ፡ የሚገልጸው ፡ የፍትሕ ፡ አስተያየት ፡ ነው ። ሁለተኛው ፤ በሕግ ፡ በተደረሰበት ፡ ጥፋት ፡ መሠረት ፡ ሊሰጠው ፡ የሚገባውን ፡ የቅጣት ፡ መጠን ፤ የሚወስነው ፡ የፍትሕ ፡ አስተያየትና ፡ ውሳኔ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ሁለቱ ፡ ውሳኔዎች ፡ ባንድነት ፡ አንድ ፡ የተሟላ ፡ የፍርድ ፡ አካል ፡ ይሆናሉ ፤ ማለት ፡ ነው ። ባጭሩ ፡ አንደኛው ፡ ክፍል ፡ የጥፋቱን ፡ ዐይነት ፡ የሚገልጽ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ፡ የቅጣቱን ፡ መጠን ፡ የሚወስን ፡ የፍርድ ፡ አስተያየት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የመጀመሪያው ፡ ውሳኔ ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔ ፤ ሁለተኛው ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ በማለት ፡ ይገለጻል ። ይኸውም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ውስጥ ፡ «ጥፋተኛ ፡ ነው ፡ የተባለበት ፡ ውሳኔ» ፡ በማለት ፡ የተጻፈውን ፡ ለማሳጠር ፡ እንዲቻል ፡ «የፍትሕ ፡ ውሳኔ» ፡ በማለት ፡ ይተካል ፡ ማለት ፡ ነው ። *)

እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ጉዳይ ፡ ብንመለስ ፤ አንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ ሊሠራ ፡ የማይቻልበት ፡ ምክንያት ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። አንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) በግልጽ ፡ እንደሚያስረዳው ፡ በመጀመሪያ ፡ ይግባኝ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤

* በዚህ ፡ ክፍለ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ የታተው ፡ በሙሉ ፡ የተርጓሚው ፡ ሐሳብ ፡ ነው ።

ከጠቅላላው ፡ ፍርድ ፡ ውስጥ ፡ ከሁለት ፡ አንዱን ፡ በመለየት ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔውን ፡ ወይም ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔውን ፡ ቢያጸድቅ ፤ ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ሊወሰድ ፡ የሚቻለው ፡ በሙሉው ፡ ፍርድ ፡ ሳይሆን ፤ ባንዱ ፡ በተለወጠው ፡ የፍርድ ፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህም ፡ ማለት ፡ በፍትሕ ፡ ውሳኔው ፡ ወይም ፡ በቅጣት ፡ ውሳኔው ፡ ብቻ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የአንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) እና ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) ሐሳቦች ፡ አንድነት ፡ ሲታዩ ፤ ይግባኝ ፡ ሊወሰድ ፡ የሚቻለው ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) ውስጥ ፡ የተጠቀሰው ፡ ግዴታ ፡ ሲፈጸም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ከሚል ፡ አስተያየት ፡ የደርሳል ። ይህም ፡ አስተያየት ፡ ሕጉ ፡ መዠመሪያ ፡ ለምክር ፡ ቤቱ ፡ በቀረበበት ፡ ጊዜ ፤ በረቂቁ ፡ ውስጥ ፡ ተጠቅሶ ፡ በነበረው ፡ የሕግ ፡ አርቃቂው ፡ ሐሳብ ፡ የተደገፈ ፡ ነው ።

የአንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) ረቂቅ ፡ ሐሳብ ፡ ለምክር ፡ ቤቱ ፡ በቀረበበት ፡ ጊዜ ፤ አንድ ፡ ጉዳይ ፡ ለሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ሊያልፍ ፡ የሚችለው ፡ ክሱ ፡ የተነሳበትን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ የመዠመሪያ ፡ ይግባኝ ፡ የለወጠው ፡ እንደሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ አሁን ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) የተጠቀሰውን ፡ ሐሳብ ፡ ያዘለ ፡ ነበር ። ምክር ፡ ቤቱ ፡ ግን ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ይግባኝ ፡ ማግኘት ፤ በመጀመሪያ ፡ ይግባኝ ፡ በተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ መወሰን ፡ አይኖርበትም ፡ በማለት ፤ ይህንን ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) ረቂቅ ፡ ሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ ተጠቅሶ ፡ የነበረውን ፡ ሐሳብ ፡ ሠረዘው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይኸው ፡ ሐሳብ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) የተጠቀሰ ፡ ስለሆን ፤ ምክር ፡ ቤቱ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ መግደፉ ፡ ዋጋ ፡ እንዳልነበረው ፡ አልተገነዘበም ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) ውስጥ ፡ ተጠቅሶ ፡ የነበረው ፡ ሐሳብ ፡ ቢገደፍም ፡ ባይገደፍም ፤ አንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) እስካለ ፡ ድረስ ፤ «ልዩ ፡ የሕግ ፡ አነጋገር ፡ ጠቅላላውን ፡ የሕግ ፡ ሐሳብ ፡ አይሽረውም ፡ P. C. (specialia generalibus derogant) በሚል ፡ የሕግ ፡ ፍልስፍና ፡ አስተያየት ፡ መሠረት ፡ ሲታይ ፤ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ለመውሰድ ፡ ሌላ ፡ ግዴታ ፡ መኖሩ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። የምክር ፡ ቤቱን ፡ ፍላጐት ፡ ለመፈጸም ፡ የሚቻለው ፡ የአንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) ረቂቅ ፡ ከተሻሻለ ፡ በኋላ ፤ አንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) አብሮት ፡ ቢሠረዝ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ስለዚህ ፡ በማናቸውም ፡ ክስ ፡ ውስጥ ፡ በፍትሕ ፡ ውሳኔና ፡ በቅጣት ፡ ውሳኔዎች ፡ ባንድነት ፡ ይግባኝ ፡ መውሰድ ፡ ይህንን ፡ ያህል ፡ በግዴታ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ። ከላይ ፡ በተገለጸው ፡ መሠረት ፡ ከሁለት ፡ አንደኛው ፡ ቢለወጥ ፡ በተለወጠው ፡ የፍርዱ ፡ ክፍል ፡ ለይቶ ፡ ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ለመውሰድ ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በፍጹም ፡ ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ለመውሰድ ፡ የማይቻልበት ፡ ክስ ፡ ሊኖር ፡ ይችላልን ? አዎን ፤ ያለ ፡ ይመስላል ። ምክንያቱም ፤ በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) ፡ መሠረት ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰጠውን ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔ ፡ ብቻ ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ ካጸደቀው ፤ ሁለት ጊዜ ፡ በመጽደቁ ፡ ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ሊወስድ ፡ አይቻልም ። እንዲሁም ፡ የወረዳው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወሰነውን ፡ ቅጣት ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ካጸደቀው ፡ ለሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ሊተላለፍ ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ በወረዳ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰጡት ፡ ሁለቱም ፡ ውሳኔዎች ፡ ማለት ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔና ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ በመጀመሪያ ፡ ይግባኝ ፡ (በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት) ፡ ከጸደቁ ፤ በሁለቱም ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ሊወሰድ ፡ ስለማይቻል ፤ በፍጹም ፡ ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ሊወሰድ ፡ የማይቻልበት ፡ ጉዳይ ፡ መኖሩ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ምክር ፡ ቤቱ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የነበረውን ፡ ሐሳብ ፡ ሲያሻሽል ፤ የሕጉ ፡ ውጤት ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ እንዲሆን ፡ አስቦ ፡ አልነበረም ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ውጤት ፡ የምክር ፡ ቤትን ፡ ሐሳብ ፡ የሚያፈርስ ፡ መሆኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ ጉዳዩ ፡ ያለበት ፡ ሁኔታ ፡ ይህ ፡ ከሆነና ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) በጸደቀበት ፡ ጊዜ ፡ የተሰጠውን ፡ የምክር ፡ ቤቱን ፡ ፍላጎት ፡ ለመፈጸም ፡ ከተፈለገ ፤ አንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫)

ከሚሰጠው ፡ ተቃራኒ ፡ ሐሳብ ፡ ጋር ፡ አመዛዝኖ ፡ በአተረጓጎም ፡ የሚሻለውን ፡ መርጦ ፡ መወሰኑ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ሲታይ ፡ የሕጉ ፡ ቃል ፡ የማያሻማና ፡ የተጣራ ፡ ፍቺ ፡ ያለው ፡ በመሆኑ ፤ በትርጉም ፡ ዘዴ ፡ ለማሻሻል ፡ ወደ ፡ አንቀጹ ፡ ታሪካዊ ፡ ምንጭ ፡ ገብቶ ፡ መመራመር ፡ አያስፈልግም ። አንድ ፡ ጽሑፍ ፡ በቀጥታ ፡ አስተያየት ፡ (በሎጂክ) ፡ ሲጠና ፡ የሚሰጠው ፡ ሐሳብ ፡ የተጣራ ፡ እስከሆነ ፡ ድረስ ፤ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ያልፈለገውን ፡ ሐሳብ ፡ ይዞ ፡ ቢገኝ ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ በማሻሻያ ፡ ሕግ ፡ ያስተካክለው ፡ እንጂ ፤ የቃላቶቹ ፡ ቀጥታ ፡ ፍቺ ፡ በግልጽ ፡ ከሚሰጠው ፡ ሐሳብ ፡ ውጭ ፡ ለማምጣት ፡ በማለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በትርጉም ፡ ለማሻሻል ፡ መሞከር ፡ የለበትም ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ ተቀባይ ፡ ካገኘ ፡ ምንም ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ያልፈቀደውና ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ ያልጠበቀው ፡ ውጤት ፡ ቢሆንም ፤ በመጀመሪያ ፡ ይግባኝ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ አንድ ፡ ክስ ፡ ተወስኖ ፡ ሊቀር ፡ መቻሉን ፡ ያስረዳል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፤ አንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) የተነገረውን ፡ ሐሳብ ፡ ስለሚያፈርስና ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) ውስጥ ፡ የተጠቀሰው ፡ ግዴታ ፡ እስከምን ፡ ድረስ ፡ እንደሆነ ፡ በጣም ፡ ግልጽ ፡ ስላልሆነ ፤ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ በማናቸውም ፡ ደረጃ ፡ ስለይግባኝ ፡ አወሳሰድ ፡ የሚወሰን ፡ ግዴታ ፡ መደረግ ፡ ላይኖርበት ፡ ነው ። አንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) ሲጸድቅ ፡ ለምክር ፡ ቤቱ ፡ ጥናት ፡ መሠረት ፡ የሆነው ፡ ይግባኝ ፡ እንዳይበዛ ፡ የመከላከል ፡ ፍላጐት ፡ ነበር ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። አሁንም ፡ ይህንኑ ፡ አስተያየት ፡ ዋና ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ቢጠና ፡ ይግባኝ ፡ መውሰድ ፡ ከሚያስፈልገው ፡ ይበልጥ ፡ እስካልበዛ ፡ ድረስ ፡ ከአንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) ፍላጐት ፡ ጋር ፡ ቢፋለስም ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ክሱ ፡ የተነሳበትን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ የመጀመሪያ ፡ ይግባኝ ፡ በሙሉ ፡ አጽድቆታል ፡ በማለት ፤ በማናቸውም ፡ ሁኔታ ፡ ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ መከልከል ፡ አይገባም ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ ይቀርብ ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ ሁለተኛው ፡ አስተያየት ፡ ቢጸድቅ ፤ በአንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ የፍርድ ፡ ሐሳብ ፡ በከፊል ፡ ወይም ፡ (አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሊኖር ፡ ስለሚችል) ፡ በሙሉ ፡ ቢጸድቅም ፤ ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ለመውሰድ ፡ ዕድል ፡ ይኖራል ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ሐሳብ ፡ ለመደገፍ ፡ የመጀመሪያ ፡ ይግባኝ ፡ በሙሉ ፡ ፍርዱን ፡ ካልለወጠ ፤ ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ አይወሰድም ፡ በማለት ፡ ሕጉ ፡ በግልጽ ፡ ለይቶ ፡ ስለማይናገር ፡ መቼውንም ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ከሁለት ፡ ይግባኝ ፡ አይብለጥ ፡ እንጂ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) እና ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) የተመለከቱትን ፡ ሐሳቦች ፡ በትርጉም ፡ በማስፋፋት ፤ የምክር ፡ ቤቱን ፡ ፍላጐት ፡ በውስጡ ፡ ለማግባት ፡ ይቻላል ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ።

ምክንያቱም ፡ የምክር ፡ ቤቱ ፡ ፍላጐት ፡ ዝቅተኛም ፡ ሆነ ፡ ከፍተኛ ፡ የይግባኝ ፡ ብዛት ፡ ከሁለት ፡ እንዳያልፍ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ከሁለት ፡ አይነስ ፤ ከሁለት ፡ አይብለጥም ፡ የሚል ፡ ነው ።

ሆኖም ፡ ሁሉንም ፡ አመዛዝኖ ፡ በመመልከት ፤ የመዠመሪያው ፡ ትርጉም ፡ ብልጫ ፡ አስተያየት ፡ ሊያገኝ ፡ ይገባዋል ። ምክንያቱም ፡ ከሕጉ ፡ ቃላት ፡ ውስጥ ፡ በትክክለኛ ፡ አስተያየት ፡ የተለመደውን ፡ ፍቺ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ሳያሻማ ፡ በግልጽ ፡ የሚደርስበትን ፡ የሕግ ፡ ሐሳብ ፡ አሻሽሎ ፤ ያልተነገረውን ፡ ሐሳብ ፡ ማፍለቅ ፤ በጣም ፡ የሚጐዳ ፡ የአተረጓጐም ፡ ልምድ ፡ መክፈት ፡ ይሆናል ። እርግጥ ፡ ነው ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ ሥር ፡ ሊኖሩ ፡ የሚችሉትን ፡ ልዩ ፡ ሁኔታዎች ፡ አሰላስሎ ፡ በመረዳት ፡ እንደሚታየው ፡ ሁሉ ፤ ይህ ፡ ትርጉም ፡ ከተሠራበት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፹፪ ፡ (፪) የሚመለከታቸው ፡ ሕጋዊ ፡ ጉዳዮች ፡ በጣም ፡ ያነሱ ፡ መሆናቸው ፡ የታመነ ፡ ነው ።

## ምሳሌዎች ፤

ከዚህ ፡ በታች ፡ ስለተጠቀሱት ፡ አስተያየቶች ፤ የሚከተለውን ፡ ሁኔታ ፡ በምሳሌ ፡ እንውሰድ ። አቶ ፡ ሀ ፡ የሥርቆሽ ፡ ክስ ፡ ቀርቦበት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፴ ፡ መሠረት ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተፈርዶበት ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔም ፡ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ቀላል ፡ እሥራት ፡ ተወስኖበታል ፡ እንበል ።

### ፩ኛ ፤ ስለ ፡ ፍትሕ ፡ ውሳኔ ፡ ብቻ ፡ ይግባኝ ፡ ቢል ።

አቶ ፡ ሀ ፡ ይግባኝ ፡ ያለው ፡ ከወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ውስጥ ፡ የቅጣቱን ፡ ውሳኔ ፡ ትቶ ፡ በፍትሕ ፡ ውሳኔው ፡ ብቻ ፡ ቢሆን ፤ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) በግልጽ ፡ ባይሆንም ፡ አነጋገሩ ፡ የሚሰጠውን ፡ ሐሳብ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔውን ፡ ያጸድቅ ፡ ይሆናል ፡ ወይም ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፪) ሐ/ን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ አቶ ፡ ሀን ፡ በነፃ ፡ ይለቀው ፡ ይሆናል ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሊፈጠሩ ፡ የሚችሉትን ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታዎች ፡ እስቲ ፡ እንመራመር ፤

(ሀ) ምንም ፡ እንኳን ፡ አቶ ፡ ሀ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ በልጽግና ፡ ሐሳብ ፡ የሌለው ፡ በመሆኑ ፡ ሌባ ፡ ሊያሰኘው ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ቢረዳም ፤ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔውን ፡ ለውጦ ፡ ወንጀለኛነቱን ፡ በማሻሻል ፤ እንበል ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫን ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፴፬ን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፤ በሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ በመጠቀሙ ፡ ጥፋተኛ ፡ የሚያደርገው ፡ አይመስልም ።

በሌላ ፡ አነጋገር ፡ ሲወሰድ ፤ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፲፫ ፡ (፪) የተመለከተው ፡ ደንብ ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ። ይኸውም ፡ የይግባኝ ፡ ሰሚው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከሳሹ ፡ በመዝገመሪያ ፡ ሲከሰስ ፡ ለማማረጫ ፡ እንዲሆን ፡ ክሱ ፡ ከቀረበበት ፡ ጋር ፡ አጣምሮ ፡ ያላቀረበውን ፡ ሌላ ፡ ጥፋት ፡ (ምንም ፡ ከቀረበበት ፡ ክስ ፡ አነስተኛ ፡ ቢሆንም) ፡ በይግባኝ ፡ በቀረበበት ፡ ተክቶ ፡ በአነስተኛው ፡ መሠረት ፡ ሊወሰን ፡ አይችልም ፡ ማለት ፡ ነው ። ለክርክር ፡ ያህል ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፲፫ ፡ (፪) በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ሊሠራበት ፡ ይቻላል ፡ ብንልም ፤ በቅጣት ፡ ረገድ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊሰጥ ፡ የሚችለውን ፡ ውሳኔ ፡ ለመረዳት ፡ አይቻልም ። ምክንያቱም ፡ ምንም ፡ አንቀጽ ፡ ፮፻፴፬ ፡ የሚወስነው ፡ ከፍተኛ ፡ ቅጣት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ቀላል ፡ እሥራት ፡ ቢሆንም ፤ በይግባኙ ፡ ላይ ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ጉዳይ ፡ ያልቀረበ ፡ ስለሆነና ፤ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) እንደሚያዘው ፤ በይግባኝ ፡ የቀረበው ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔው ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፤ መጀመሪያ ፡ የሰማው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፤ የይግባኙ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ለመለወጥ ፡ ስለማይችል ፤ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወሰነውን ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ ቅጣት ፡ ለመቀነስ ፡ አይችልም ።

(ለ) የፍትሕ ፡ ውሳኔውን ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያጸደቀ ፡ እንደሆን ፡ ደግሞ ፤ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፫) በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ለመውሰድ ፡ አይቻልም ። የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ በከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ ያልተነሣ ፡ ጉዳይ ፡ ከሆነ ፤ ይኸውም ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔውን ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ካጸደቀው ፡ በኋላ ፡

ቢሆን ፤ አቶ ፡ ሀ ፡ አውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሰጠው ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ ማለት ፡ አይገባውም ።

(ሐ) አቶ ፡ ሀ ፡ በከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ነጻ ፡ ቢለቀቅ ፡ ደግሞ ፤ ሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ለጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ሊል ፡ ይችላል ። የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፤ ነፃ ፡ እንዲወጣ ፡ የተሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ ገልብጦ ፡ የአቶ ፡ ሀን ፡ ጕዳይ ፡ እንደገና ፡ ያያል ፡ ወይም ፡ እንዲታይ ፡ ያደርጋል ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ አቶ ፡ ሀ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፪)ን መሠረት ፡ በማድረግ ፡ «ሕግ ፡ በሚያዘው» ፡ ቅጣት ፡ ይወሰንበታል ። የአቶ ፡ ሀን ፡ ጕዳይ ፡ እንደገና ፡ የሚያየው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰጠውን ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ጨምሮ ፡ እንበል ፡ ለአምስት ፡ ዓመት ፡ ከከባድ ፡ እሥራት ፡ ጋር ፡ ቢያደርግ ፤ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ የሚከለክለው ፡ ደንብ ፡ የለም ። እንደገና ፡ ጕዳዩን ፡ የሚያየው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቅጣቱን ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ መጠን ፡ ለመለወጥ ፡ ከቻለና ፤ ለማክበድ ፡ በአውራጃ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ የማይታገድ ፡ ከሆነ ፤ ለአቶ ፡ ሀ ፡ ቀድሞውኑ ፡ የይግባኙ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ አውራጃው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወስኖበት ፡ በቅጣቱ ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ የይግባኝ ፡ መብት ፡ ቢከለክለው ፡ ኑሮ ፤ ከሚኖረው ፡ ሁኔታ ፡ የተለየ ፡ ነገር ፡ አላጋጠመውም ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህንን ፡ ሁኔታ ፡ ለመከላከል ፡ እንዲቻል ፤ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ በይግባኝ ፡ ውስጥ ፡ የቀረበ ፡ ባልሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፤ ሁለተኛው ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሁለቱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አስተያየት ፡ ትክክለኛ ፡ የመሰለውን ፡ መርጦ ፡ ወሳኝ ፡ ቢሆን ፡ የሚሻል ፡ ይሆናል ። ይህንንም ፡ ሲያደርግ ፡ ከበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ስለወንጀሉ ፡ ትክክለኛ ፡ ውሳኔ ፡ የሰጠውን ፡ መርጦ ፡ ይለያል ። ይህም ፡ የሚረዳው ፡ ከበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያንደኛው ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔ ፡ ከጸደቀ ፤ ያለ ፡ ሌላ ፡ ውሳኔና ፡ ክርክር ፡ በቅጣትም ፡ ረገድ ፡ የዚያኑ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ አብሮት ፡ እንዲወሰድ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። ይህም ፡ ቢሆን ፡ ሁለተኛ ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይህንን፡ ብቻ ፡ እንዲያደርግ ፡ ከተፈለገ ፤ «በሕግ ፡ መሠረት» ፡ ቅጣት ፡ የሚወስን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ሊገመት ፡ ላይችል ፡ ነው ። ከዚሁም ፡ በላይ ፤ የሁለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተግባር ፡ የተሻለውን ፡ ውሳኔ ፡ መምረጥ ፡ ይሁን ፡ የሚለው ፡ አስተያየት ፤ በግዴታ ፡ ለፍትሕ ፡ ውሳኔ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በቅጣት ፡ ውሳኔም ፡ ረገድ ፡ ተቃራኒ ፡ አስተያየቶች ፡ ሲኖሩም ፡ መሆን ፡ ሊኖርበት ፡ ነው ። ይህ ፡ ከሆነ ፡ ደግሞ ፤ በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፪) መ/ ከተመለከተው ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ የሚፋለስ ፡ ይሆናል ። ምክንያቱም ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ እንደሚያዘው ፤ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ ሲቀርብለት ፤ ያጸድቃል ፤ ይጨምራል ፤ ወይም ፡ ያሳንሳል ፡ እንጂ ፤ ከበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ባንዱ ፡ የተሰጠውን ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ለማጽደቅ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። በኋለኛው ፡ የቀረበውን ፡ ተቃራኒ ፡ ክርክር ፡ ለማሸነፍ ፤ ምናልባት ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፭ ፡ (፪) መ/ የተጠቀሰው ፡ ደንብ ፡ የሚሠራው ፡ በመጀመሪያ ፡ ይግባኝ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ለመመለስ ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። ሆኖም ፡ ይህንን ፡ አስተያየት ፡ የሚደግፍ ፡ ሕግ ፡ የለም ።

፪ኛ ፤ ስለተወሰነበት ፡ ቅጣት ፡ ብቻ ፡ ይግባኝ ፡ ቢል ።

በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፩ ፡ (፪) (መ) መሠረት ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የቅጣቱን ፡ ውሳኔ ፡ ይደግፈው ፤ ያበዛው ፤ ወይም ፡ ያሳንሰው ፡ ይሆናል ። በዚህን ፡ ጊዜም ፡ ሊፈጠሩ ፡ የሚችሉትን ፡ የሕግ ፡ ሁኔታዎች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እስቲ ፡ እናጥና ።

(ሀ) የቅጣቱን ፡ ውሳኔ ፡ ቢያጸድቀው ፤ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥር ዓት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፺፩ ፡ (፫) መሠረት ፤ ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ። በተጨማሪ ፤ የፍትሕ ፡ ውሳኔ ፡ በይግባኙ ፡ ውስጥ ፡ የቀረበ ፡ ጉዳይ ፡ ስላልሆነ ፤ ተከሣሹ ፡ ወይም ፡ ሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ስለፍትሕ ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ ሊሉ ፡ የሚችሉ ፡ አይመስልም ።

(ለ) የቅጣቱ ፡ ውሳኔ ፡ በማሳነስም ፡ ሆነ ፡ በማብለጥ ፡ ቢለወጥ ፡ ደግሞ ፤ ሕግ ፡ አስከባሪውና ፡ ተከሣሹ ፡ ሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ለመውሰድ ፡ ስለሚችሉ ፤ ጠቅ ላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ልክ ፡ ከከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሻለ ፡ ቦታ ፡ አይኖረውም ። ይኸውም ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በይግባኝ ፡ ሥልጣኑ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ቅጣ ቱን ፡ ያጸድቅ ፡ ይጨምር ፡ ወይም ፡ ያሳንስ ፡ ይሆናል ፡ ማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ በክፍል ፡ ነገር ፡ ፩ኛ ፡ (ለ) የተነገረው ፡ ሐሳብ ፡ እዚህም ፡ የሚ ገባ ፡ ነው ። በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ተመሠረተ ፡ ድረስ ፤ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በመጀመሪያ ፡ ይግባኝ ፡ የተሰጠ ውን ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ለመጨመር ፡ ወይም ፡ ዓይነቱን ፡ ለመለወጥ ፡ የሚያ ግደው ፡ ሕግ ፡ የለም ። ሆኖም ፡ ይግባኝ ፡ በተከሳሽ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ሕጉ ፡ የተከሣሽን ፡ ጥቅምና ፡ ጉዳት ፡ የሚመለከት ፡ አይደለም ። በመጀመሪያው ፡ ይግባኝ ፡ ላይ ፡ ባይሆንም ፡ ቅሉ ፡ (ምክንያቱ ፡ ከሥር ፡ ከሰማው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ጋር ፡ ቢለይም ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ ስላልሆነ) ፡ ሁለተኛ ፡ ይግ ባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከፍተኛ ፡ ቅጣትን ፡ ሲሰጥ ፤ ይህ ፡ የመጨረሻውንና ፡ ሁለ ተኛውን ፡ ይግባኝ ፡ የሚመለከት ፡ በመሆኑ ፤ የመጀመሪያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ቢወሰን ፤ የይግባኝ ፡ ባይ ፡ ተከሣሽን ፡ ቅጣት ፡ ማከ በድ ፡ (reformatio in pejus) እንዳይኖር ፡ ለማድረግ ፡ ይረዳል ።

፫ኛ ፤ ስለ ፡ ፍትሕ ፡ ውሳኔና ፡ ስለ ፡ ቅጣት ፡ ውሳኔ ፤ ማለት ፡ ስለ ፡ ሁለቱም ፡ ውሳኔዎች ፡ ይግባኝ ፡ ቢል ።

ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፺፩ ፡ (፪) (ለ) (፩) መሠረት ፤ የፍትሕ ፡ ውሳኔውንና ፡ የቅጣቱን ፡ ውሳኔ ፡ ገልብጦ ፡ ተከሣሽን ፡ በነፃ ፡ ይለቅ ፡ ይሆናል ፤ ወይም ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔውን ፡ ለውጦም ፡ ሆነ ፡ ሳይ ለውጥ ፤ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፺፩ ፡ (፪) (ለ) (፪) መሠረት ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔውን ፡ ይደግፍ ፤ ወይም ፡ ይጨምር ፤ ወይም ፡ ያሳንስ ፡ ይሆ ናል ። በዚህም ፡ እርእስት ፡ ሥር ፡ ሊፈጠሩ ፡ የሚችሉትን ፡ የሕግ ፡ ሁኔታዎች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እንመልከት ።

(ሀ) ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔውንና ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔውን ፡ ገል ብጦ ፡ ተከሣሽን ፡ በነፃ ፡ ቢያወጣ ፤ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ይግባኝ ፡ ሊል ፡ ይችላል ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሊፈጠር ፡ የሚችለው ፡ ሁኔታ ፡ ከላይ ፡ በክፍለ ፡ ነገር ፡ ፩ኛ ፡ (ለ) የታተተውን ፡ አስተያየት ፡ የሚመለከት ፡ ነው ።

(ለ) ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔውን ፡ ብቻ ፡ ለውጦ ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔውን ፡ ያጸድቅ ፡ ይሆናል ። ለምሳሌ ፤ አድራጎቱ ፡ ሥርቆሽ ፡ ሳይሆን ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ሀብት ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ብልጽግና ፡ ለማግኘት ፡ መሆኑን ፡ በመረዳት ፤ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አንቀጽ ፡ ፩፻፲፫ ፡ (፪)ን ተከትሎ ፤ ከሥርቆት ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ ቅጣት ፡ በሚያዘው ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፮፻፵፩ ፡ መሠረት ፤ አቶ ፡ ሀን ፡ እምነት ፡ በማጉደል ፡ ጥፋተኛ ፡ ያደረገ ፡ እንደሆን ፡ ተከሣሹም ፡ ሆነ ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ስለ ፡ ቅጣቱ ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ ሊሉ ፡ አይችሉም ። አቶ ፡ ሀ ፡ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ነፃ ፡ እንዲለቀው ፡ በማለት ፡ ስለ ፡ ፍትሕ ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ ሊል ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ ሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ስለ ፡ ፍትሕ ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ ሊል ፡ ይችላል ። ሆኖም ፡ የቅጣቱን ፡ ውሳኔ ፡ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ማይለውጠው ፡ ሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ይህንን ፡ የሚያደርግበትን ፡ ምክንያት ፡ ለመረዳት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ከሁሉ ፡ ይበልጥ ፡ ትክክሉ ፡ አቶ ፡ ሀ ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፰ ፡ (፪) (ሀ) መሠረት ፡ በሌብነት ፡ ሳይፈረድበት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በአንቀጽ ፡ ፩፻፺፰ ፡ (፪) መሠረት ፡ እምነት ፡ በማጉደሉ ፡ ቢፈረድበት ፤ ሕግ ፡ አስከባሪው ፡ ይግባኝ ፡ አይወስድም ፡ በሚል ፡ አስተያየት ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔውን ፡ መለወጡ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አስተያየት ፡ ተቀባይ ፡ የሚያገኝ ፡ አይመስልም ። ምክንያቱም ፡ ከአንቀጽ ፡ ፩፻፺፰ ፡ (፫) ጋር ፡ ስለሚፋለስ ፡ ነው ።

(ሐ) ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔን ፡ ቢለውጥ ፡ (ከሌብነት ፡ ወደ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነ ፡ ብልጽግና) ፡ እና ፡ እንዲሁም ፡ የቅጣት ፡ ውሳኔን ፡ ወደ ፡ ፈለገው ፡ ቢለውጥ ፤ ስለ ፡ ፍትሕና ፡ ስለ ፡ ቅጣት ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ ለመውሰድ ፡ በመቻሉ ፤ ጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከላይ ፡ በክፍለ ፡ ነገር ፡ ፩ኛ ፡ (ሐ) እና ፡ ፪ኛ ፡ (ለ) የተመለከቱትን ፡ ማብራሪያና ፡ ምሳሌዎች ፡ ተመልከት ።

(መ) ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሁለቱንም ፡ የፍትሕን ፡ ውሳኔና ፡ የቅጣትን ፡ ውሳኔ ፡ ካጸደቀ ፤ የሁለተኛ ፡ ይግባኝ ፡ ዕድል ፡ በሙሉ ፡ የተዘጋ ፡ ይሆናል ።

(ሠ) ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የፍትሕ ፡ ውሳኔውን ፡ ደግፎ ፤ የቅጣቱን ፡ ውሳኔ ፡ በማብለጥ ፡ ወይም ፡ በማሳነስ ፡ ቢለውጥ ፤ የሚኖረው ፡ ውጤት ፡ ከላይ ፡ በክፍለ ፡ ነገር ፡ ፪ኛ ፡ (ለ) ከተነገረው ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ በመሆኑ ፤ ተመሳሳይ ፡ አስተያየትን ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው ።

## ማሠርያ ፤

እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ አጥጋቢ ፡ ላይሆኑ ፡ ይችላሉ ። ነገር ፡ ግን ፤ ግልጽ ፤ ትክክልና ፡ ተስማሚ ፡ ስለሆኑ ፤ የሚያስፈልገው ፡ መሻሻል ፡ ሁሉ ፡ በምክር ፡ ቤት ፡ መደረግ ፡ ይኖርበታል ፡ እንጅ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መሆን ፡ የለበትም ።